AMHARIC

# የዩናይትድ ስቴትስ ካፒቶልና ኮንግረስ



# ካፒቶል



ሴኔተር ሄንሪ ክሌይ የ1850ን የማቻቻል ሀሳብ በመደገፍ በአሮጌው የሴኔት ምክር ቤት ንግግር ሲያደርግ።

የዩናይትድ ስቴትስ ካፒቶል በዓለም በሰፊው ዕውቅና ያተረፈ የዲሞክራሲ አስተዳደር ተምሳሌት ነው። ከ1800 ጀምሮ የኮንግረስ መቀመጫ ሆኖ አገልግሏል። ኮንግረስ የአገሪቱን ሕግጋት ለማውጣት የሚሰበሰበው በካፒቶል ነው። የፕሬዚደንቶች በዓለ ሲመት የሚካሄደውና አገሪቱ ያለችበትን ሁኔታ አስመልክተው ንግግራቸውን የሚያቀርቡት በዚህ ሥፍራ ነው። ካፒቶል ከሁለት ምዕተ ዓመታት በላይ ከአገሪቱ ጋር አብሮ አድጓል፤ አዳዲስ ግዛቶች የአገሪቱ አካል እየሆኑ በመጡ ቁጥር እነሱን የሚወክሉ ሴኔተሮችና የሕዝብ እንደራሴዎች ለማስተናገድ እንዲችል ተጨማሪ ተቀጥላዎች በሕንጻው ታክሏል። ኮርኒሶቹ በታሪካዊ ምስሎች የተሞላ ሲሆን፣ ግድግዳዎቹ ከአገሪቱ ታሪክ በተቀዱ ታላላቅ የታሪክ ምዕራፎችና ህዝባዊ ክስተቶችን በሚያሳዩ ቅርጻ ቅርጾችና ስዕሎች የተሞላ ነው።

## የካፒቶል ጅማሬ

ዶ/ር ዊሊያም ቶርንቶ የመጀመሪያውን የካፒቶል ንድፍ አውጪ ነው፤ የመሠረት ድንጋዩ የተጣለው ደግሞ በሴፕቴምበር 18 ቀን 1973 በጆርጅ ዋሽንግተን ነበር። ቤንጃሚን ሄንሪ ላትሮብና ቻርልስ ቡልፊንች ከሌሎች የኪነ ሕንጻ ባለሙያዎች ጋር በጋራ በመሆን ግንባታውን መርተዋል። በ1800 መንግሥት በፊላዴልፊያ ከነበረው ጊዜያዊ መቀመጫው ወደ ዋሽንግተን ዲሲ በተዘዋወረ ጊዜ ካፒቶል ገና ሥራው ያልተጠናቀቀ፣ በጡብና በአሸዋ ድንጋይ የተሰራ ሕንጻ ነበር። የህዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት ትንሽና በተጣበበው ኖርዝ ዊንግ ተብሎ በሚጠራው ህንፃ መገልገል ጀመረ። በመጀመሪያ የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት ስብሰባ የተካሄደው የኮንግረስ ቤተ መጽሐፍት እንዲሆን ታስቦ በነበረው በሁለተኛው ፎቅ በሚገኝ ሰፊ አዳራሽ ውስጥ ነበር፤ ሴኔቱ ደግሞ የተሰበሰበው በምድር ቤት በሚገኝ አንድ ክፍል ውስጥ ነበር። ከ1810 እስከ 1859 ባሉት አመታት ሴኔቱ ጉባዔውን ያካሄደው አሁን አሮጌው የሴኔት አዳራሽ በመባል በሚታወቀው ክፍል ውስጥ ነበር።



በብሔራዊ የስዕል ጋለሪ ስብስብ የሚገኘው በሳሙኤል ሞርስ የተሳለው አሮጌው የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት አዳራሽ ስዕል።

በ1807 ለሕዝብ እንደራሴዎች እንዲያገለግል ሆኖ የካፒቶል ደቡባዊ ተቀጥላ ሕንጻ ተጠናቀቀ። ለባለ ጉልላቱ ማዕከላዊ ሕንጻ ተመድቦ በነበረው ባዶ ቦታ የሕዝብ እንደራሴዎችና የሴኔት ሕንጻዎችን የሚያገናኝ ባለእንጨት መተላለፊያ ተሰርቶበታል። በኦገስት 1814 አሜሪካ ከታላቋ ብሪታኒያ ጋር ለሁለተኛ ጊዜ በጦርነት ላይ ሳለች የታላቋ ብሪታኒያ ወታደሮች ካፒቶልንና ሌሎች በዋሽንግተን የሚገኙ የመንግሥት ሕንጻዎችን ባቃጠሉበት ጊዜ ካፒቶል ይህን ይመስል ነበር። ውጫዊ ግድግዳዎቹ ቢተርፉም እንኳን፣ አብዛኛዎቹ የውስጥ ክፍሎች ግን ወድመዋል።

በ1819 በድጋሚ የተገነቡት የካፒቶል ተቀጥላ ሕንጻዎች በድጋሚ ተከፈቱ። ማዕከላዊው ሕንጻ ደግሞ በ1826 ተጠናቆ ሁለቱንም ተቀጥላ ሕንጻዎች አገናኝቷል። በክብ ቅርጽ የተሰራው ሕንጻ ጎልላት በእንጨትና በነሀስ የተሸፈነ ነበር።

## የካፒቶል ማስፋፊያና ጉልላት

በ1850 በርካታ ተጨማሪ ግዛቶች የኅብረቱ አባላት በመሆናቸው ምክንያት የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤትና ሴኔት ይጠቀሙ ከነበሩባቸው ህንፃዎች የማስተናገድ አቅም በላይ ሆነው ነበር። በቀድሞው ሕንጻ ግራና ቀኝ ታላላቅ ተቀጥላ ሕንጻዎች እንዲሰሩና ካፒቶሉ እንዲስፋፋ ተወሰነ። በ1851 በሁለቱም

የካፒቶል የስዕል ሃብቶች ወደ ቀጣዩ ትውልድ ተጠብቀው እንዲተላለፉ እገዛ ያድርጉ። እባክዎን ስዕሎቹንና ሃውልቶቹን እያያችሁ ተደሰቱ፣ ነገር ግን አይንኳቸው።

የኮንግረስ ምክር ቤቶች ያገለገለው ዳንኤል ዌብስተር የአዲሶቹን ተቀጥላ ሕንጻዎች የመሠረት ድንጋይ ባኖረበት ጊዜ ታዋቂ የሆነውን ንግግር አድርጓል። የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት አሁን የሚገኝበትን መሰብሰቢያ የያዘው በ1857 ሲሆን፣ ሴኔቱ ደግሞ ወደ አዲሱ ምክር ቤት በ1859 ተዘዋወረ።

የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት አሮጌ አዳራሽ የኋላ ኋላ ብሔራዊ የሃውልቶች አዳራሽ እንዲሆን ተደርጓል። እያንዳንዱ ግዛት ሁለት ታላላቅ የሚላቸውን ዜጎቹን ሃውልቶች እንዲያበረክት ኮንግረስ ጋበዘ። በአሁኑ ጊዜ በዚህ መልኩ የተበረከቱት ሃውልቶች በብሔራዊ የሃውልቶች አዳራሽ፣ በሮተንዳ፣ በካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከልና በመላው ሕንጻ መተላለፊያዎች ላይ ለእይታ ቀርበዋል።

በእርስ በእርስ ጦርነቱ ጊዜ በቶማስ ዋልተር የተነደፈው አዲሱ ባለብረት ጉልላት ሥራ ቀጠለ። በዲሴምበር 2 ቀን 1863 ቶማስ ካውፎርድ በተባለው አሜሪካዊ አርቲስት የተሰራው የነጻነት ሃውልት በኢስት ፕላዛ አናት በ278 ጫማ ርቀት በጉልላቱ ላይ ተቀመጠ።

በ1870 የአትክልት ሥፍራ አርክቴክት የነበረው ፍሬድሪክ ሎው ኦልምስቴድ በሰሜን፣ ደቡብና ምዕራብ የካፒቶል ከፍታዎች ዙሪያ ያሉትን ሰገነቶች ነደፈ። እነዚህ ሰገነቶች ተጨማሪ ክፍሎች እንዲኖሩ ከማስቻላቸውም ሌላ የካፒቶል ህንፃ ያረፈበት እንደ ታላቅ መቆሚያ ሆኖ  በካፒቶል ሂል ግርጌ ተሰድሮ ይገኛል።

## ባለፈው ምዕተ ዓመት የተደረጉ ለውጦች

በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አሁንም ተጨማሪ ቦታ የግድ አስፈለገ። የመጀመሪያዎቹ የሕዝብ እንደራሴዎችና የሴኔት ቢሮዎች ሕንጻዎች የተጠናቀቁት እንደ ቅደም ተከተላቸው በ1908ና 1909 ነበር።

የካፒቶል የመጀመሪያው የአሸዋ ድንጋይ ውጫዊ ግድግዳዎች በከፍተኛ ደረጃ በመጎዳታቸው ዋነኛ የሚባል እድሳት ማድረጉ አስፈላጊ ሆነ። በ1958 እና በ1962 መካከል ምሥራቃዊው የፊት ለፊት ገጽታ በሰላሣ ሁለት ጫማ እንዲስፋፋና የፊት ለፊት ገጽታው በእምነበረድ እንዲሸፈን ተደረገ። የአሮጌው ውጫዊ ግድግዳ ክፍሎች አሁንም በምሥራቃዊ የፊት ለፊት መተላለፊያዎች ይታያሉ፤ በተጨማሪም ካፒቶል በሚገነባበት ወቅት ድንጋይ በማውጣት ሥራ ላይ ለነበሩት ባሮች አፍሪካን አሜሪካዊያን ቋሚ ማስታወሻ ሆነዋል።

በ1980ዎቹ ምዕራባዊው የፊት ለፊት ገጽታ በጥንቃቄ ታድሶ ወደ ነበረበት ሁኔታ እንዲመለስ ተደረገ፤ በእምነበረድ ያልተሸፈነው ብቸኛው ነባር የውጭ ክፍልም ይህ ነው።

በቅርብ ጊዜ በካፒቶል ላይ የተጨመረው የካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል ነው፤ የተገነባው ከምሥራቃዊው ፕላዛ በታች ሲሆን፣ በ2008 ተጠናቀቀ። በዚህ ህንፃ ውስጥ የትዕይንት አዳራሽ፣ የማስተዋወቂያ አዳራሾች፣ ሬስቶራንት፣ የስጦታ መደብሮች፣ ከላይብራሪ ኦፍ ኮንግረስ ጋር የሚያገናኝ መተላለፊያና ካፒቶል በተሻለ እንዲያገለግል የሚያደርጉ ማሻሻያዎች ይገኛሉ።




የሕዝብ እንደራሴዎች አሮጌው አዳራሽ በአሁኑ ጊዜ ብሔራዊ የሃውልቶች አዳራሽ ሆኖ ያገለግላል።

## ሮተንዳ

ሮተንዳ የካፒቶል ማዕከል ነው። በሕግ ማውጣት ሂደት የተለየ ሚና ባይኖረውም ከአብርሃም ሊንከን ጀምሮ ለፕሬዚደንቶች፣ የኮንግረስ አባላት፣ ወታደራዊ ጀግንነት ለፈጸሙና ታላላቅ ዜጎች የቀብር ስንብት ሥነ ሥርዓት የሚካሄድበት ሥፍራ ሆኖ አገልግሏል። የመራሄ መንግሥታትና ልዩ እንግዶች የአቀባበል ሥነ ሥርዓት ብዙውን ጊዜ የሚከናወነው በሮተንዳ ሕንጻ ውስጥ ነው፤ በርካታ ታሪካዊ በዓላትም በዚህ የሕንጻ ክፍል ተከብረዋል።

በሮተንዳው ህንፃ ውስጥ የጀነራል ዋሽንግተን ወታደራዊ ረዳት መኮንን በነበረው በጆን ትረምቡል የተሳሉ አራት ግዙፍ በአሜሪካ አቢዮት ወቅት የነበሩ ክስተቶችን የሚያሳዩ ስእሎች ተሰቅለዋል። በሌሎች አራት ሰዓሊያን የተሳሉ ስዕሎች ደግሞ ጥንት ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የተደረጉ አሰሳዎችንና ሰፈራዎችን የሚያሳዩ ናቸው። ከሮተንዳው ወለል 180 ጫማ ከፍ ብሎ የተሰቀለው አጎበር ላይ ደግሞ በጣሊያን አሜሪካዊው ሰዓሊ ኮንስታንቲኖ ብሩሚዲ የተሳለ ዘ አፖቴዮሲስ ኦፍ ዋሽንግተን በመባል የሚታወቅ ስዕል ይገኛል። ጆርጅ ዋሽንግተን በአሜሪካ ዲሞክራሲና የቴክኖሎጂ መሻሻል ተምሳሌቶች ተከቦ ይታያል። የካፒቶልን ብዙዎች ክፍሎችና መተላለፊያዎች ያሳመረና ስዕል የሳለባቸው ብሩሚዲ ነበር፤ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ በሮተንዳው እንደመቀነት ዙሪያውን የሚዞር የስእልና የቅርፅ ጌጦችን ይሰራ ነበር። የእርሱ ስዕሎት በአሜሪካ ታሪክ ወሳኝ የሚባሉ ምዕራፎችን የሚያሳዩ ስለነበሩ ከህልፈተ ህይወቱ በኋላ ሌሎች አርቲስቶች ስራውን አጠናቀውታል።



ኮንስታንቲኖ ብሩሚዲ በ1865 በካፒቶል ጉልላት ውስጣዊ ክፍል ዘ አፖቴዮሲስ ኦፍ ዋሽንግተን በመባል የሚታወቀውን ስእል ሳለ።

ይህ እይታ በ1800 የካፒቶል ሰሜናዊ ጎን ብቻ ተጠናቆ ባለበት ጊዜ የነበረውን ገጽታ ያሳያል። ▶





◀ በ1861 የአዲሱ ባለብረት ጉልላት ግንባታ በሚገባ በመካሄድ ላይ ነበር።

▼ ከ1801 ጀምሮ የፕሬዚደንቶች በዓለ ሲመት በካፒቶል ሲካሄድ ቆይቷል። በዚህ ምስል በ1925 የተካሄደው የካልቪን ኩሊጅ በዓለ ሲመት ይታያል።



▲ በጉልላቱ አናት ላይ የነጻነት ሐውልት ቆሟል

የመጀመሪያው አለ ተብሎ የሚታወቅ የካፒቶል ፎቶግራፍ በ1846 የተነሳ ነበር። ▶





CVC 18-095

# ኮንግረስ

የዩናይትድ ስቴትስ ኮንግረስ ሁለት ሕግ አውጪ አካላት አሉት እነርሱም ሴኔትና የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት ሲሆኑ ምክር ቤቶቹ ስብሰባዎቻቸውን በካፒቶል ሕንፃ ግራና ቀኝ ባሉ ሁለት ቅጥያዎች ውስጥ ያካሂዳሉ። አባላት የሕግ ረቂቆችን ያቀርባሉ፤ በጉዳዮቹ ላይ ንግግር ያደርጋሉ፤ በረቂቅ ሕጎች፣ ውሳኔዎች፣ የዕጩዎች ሹመትና አገሪቱ በፈረመቻቸው ስምምነቶች ላይ ድምጽ በመስጠት ውሳኔ ያሳልፋሉ። በመላው ካፒቶልና በጽሕፈት ቤቶች ሕንጻዎች ያሉ ደወሎችና መብራቶች አባላት ድምጽ እንዲሰጡ ጥሪ ያደርጉላቸዋል።

የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት ከዲሴምበር 1857 ጀምሮ በደቡቡ የሕንጻው መሰብሰቢያ አዳራሽ ሲሰበሰብ ቆይቷል። የህዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት የህግ ማውጣት እንቅስቃሴ ሂደት የሚጀመረውና ፍፃሜ የሚያገኘው በዚህ ምክር ቤት ውስጥ ነው። እያንዳንዱ የህግ ረቂቅ በመጀመሪያ የሚቀርበው እዚህ ሲሆን ለኮሚቴዎች የተመሩ የህግ ረቂቆች ክርክር እንዲደረግባቸውና ድምፅ እንዲሰጥባቸው ወደዚሁ ይመለሳሉ።

ሦስት ደረጃ ያለው ከፍ ያለ መድረክ በምክር ቤቱ ውስጥ ጎልቶ ይታያል። አፈ ጉባዔው ወይም ተወካዩ ከፍ ባለው መድረክ ላይ ሥፍራውን ይዞ በፓርላማ ስርዓት ባለሙያው እየታገዘ ስብሰባ ይመራል። በመክር ቤቱ ዝቅ ባሉ ወለሎች ላይ ረቂቅ ህጎችን ማንበብ፣ ድምፆችን መቁጠርና የሚካሄዱ ክረክሮችን መቅዳትን ጨምሮ የምክር ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴዎች እንዲካሄድ የሚረዱ ሠራተኞች ይጠቀሙበታል። በቻምበሩ የሚታየው የቲያትር አዳራሽ መሰል አቀማመጥ የተጀመረው በ1913 ነበር፤ አስቀድሞ እያንዳንዱ አባል የራሱ ዴስክ ኖሮት ይህ ዴስክ እንደ ብቸኛ የቢሮ ስፍራ ያገለግል ነበር። በ1789 ከተጸነሰበት ጊዜ ጀምሮ የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት ጋለሪዎቹን ለሕዝብና ለብዙሀን መገናኛ ክፍት አድርጓል። የሸንጎ ክርክሮቹን በቴሌቪዥን ቀጥታ ስርጭት ማድረግ የተጀመረው በ1979 ነው።

ሴኔቱ አሁን ወዳለበት በሰሜን በኩል ወዳለው ሕንጻ የተዘዋወረው በ1859 አዱሱ የካፒቶል የሰሜን ቅጥያ ከተጠናቀቀ በኋላ ነው። ሰብሳቢው አትራኖሱ ካለበት ከፍ ካለው የክብር ቦታ ይቀመጣል። ሰብሳቢው ካለበት ቦታ በታች ያሉ ስፍራዎች ለሴኔቱ መኮንኖችና ሠራተኞች የተመደበ ነው። አንድ መቶ መቀመጫዎች በግማሽ ክብ ቅርጽ በፖለቲካ ፓርቲዎች ተከፍለው ተሰድረው ይገኛሉ። በአንዳንድ በጣም አልፎ አልፎ በሚከሰቱ ሁኔታዎች ሳቢያ ካልሆነ በስተቀር ስብሰባዎች ለሕዝብ ክፍት የሚሆኑ ሲሆን በዚህም ወቅት የሴኔት ጋለሪዎች ለጋዜጠኞች፣ ለሠራተኞች፣ ለቤተሰብ አባላት፣ ለዲፕሎማቶችና ለጎብኚዎች ክፍት ይሆናሉ። ከ1986 ጀምሮ የሴኔቱ የየዕለት ስብሰባዎች በቴሌቪዥን ይተላለፋሉ።

## ሴኔት

ሴኔቱ 100 አባላት ያሉት ሲሆን እያንዳንዱ ግዛት በእኩል ደረጃ በሁለት ሴኔተሮች ይወከላል። አንድ ሴኔተር የ30 ዓመት ዕድሜ የሞላው፣ የሚወክለው ግዛቱ ነዋሪና ቢያንስ ለዘጠኝ ዓመታት የዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ ሆኖ የቆየ ሊሆን ይገባል። ሴኔተሮች ለስድስት ዓመታት አገልግሎት የሚመረጡ ሲሆን የአገልግሎት ጊዜያቸው የአንዱ በሌላው ይደረባል፤ ከሴኔት አባላት መካከል አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት በየሁለት ዓመቱ ይመረጣሉ።

ቀደም ሲል ሴኔተሮች በግዛት ሕግ አውጪዎች ይመረጡ ነበር ነገር ግን በ1913 በሕገ መንግሥቱ ላይ በተደረገው አስራ ሰባተኛው ማሻሻያ ሴኔተሮች በቀጥታ በሕዝብ እንዲመረጡ ደንግጓል። አንድ መቀመጫ ክፍት ከሆነ የአብዛኞቹ ግዛቶች ገዢዎች ተተኪውን ሴኔተር የመሾም ሥልጣን አላቸው። ምክትል ፕሬዚደንቱ "የሴኔቱ ፕሬዚደንት" ሲሆን፣ በዕለት ተዕለት ሥራ ግን የሰብሳቢነቱን ቦታ የሚይዘው በአብዛኛው ጊዜያዊ ፕሬዚደንቱ (አብዛኛውን መቀመጫ የያዘው ፓርቲ አንጋፋ) ወይም የፕሬዚደንቱ ተወካይ ነው።

## የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት

ከ20ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ጀምሮ የሕዝብ እንደራሴዎች አባላት ብዛት 435 ድምጽ በሚሰጡ እንደራሴዎች ተገድቦ ነበር። በየ10 ዓመቱ የሕዝብ ቆጠራ ከተካሄደ በኋላ  የሕዝብ ቁጥር ላይ በመመስረት ተጨማሪ መቀመጫዎች ለግዛቶች ይሰጣሉ ከዚሁም ጋር የአገልግሎት ክልሎች እንደገና ሊወሰኑ ይችላሉ። እያንዳንዱ ግዛት ቢያንስ በአንድ ተወካይ የመወከል መብት አለው።



የሴኔት ቻምበር



የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት

አንድ እንደራሴ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ወይም የአገልግሎት ጊዜ አጋማሽ ላይ ከለቀቀ ተተኪ ለመምረጥ ልዩ ምርጫ ይካሄዳል። በተጨማሪም አሜሪካን ሳሞአ፣ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ፣ ጉዋም፣ ዘ ቨርጅን አይላንድስና የሰሜን ማሪያና ደሴቶች ድምጽ በማይሰጡ እንደራሴዎች ይወከላሉ፤ ፓርቶ ሪኮ ደግሞ በአንድ ተቀማጭ ኮሚሽነር ትወከላለች።

አንድ ሰው እንደራሴ ለመሆን ቢያንስ 25 ዓመት ዕድሜ፣ የግዛቱ ነዋሪ መሆንና የዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ ከሆነ በኋላ ሰባት አመት የኖረ መሆን አለበት። የእንደራሴዎች ምክር ቤት አባላት ለሁለት ዓመታት ያገለግላሉ። የምክር ቤቱ የበላይ መኮንን አፈ ጉባዔው ነው። አፈ ጉባዔው ከምክትል ፕሬዚደንቱ ቀጥሎ የፕሬዚደንትነቱን ቦታ ለመያዝ ይችላል።

## ልዩ ሥልጣኖች

በሕገ መንግሥታዊ የመቆጣጠርና ሚዛናዊነትን የማስፈን ሥርዓት ስር ሕግ አውጪ፣ አስፈጻሚና ሕግ ተርጓሚ የመንግሥት አካላት እንዲሁም ሁለቱ የኮንግረስ አካላት የፌዴራል መንግሥቱን ሥልጣን ያጋራሉ።

ሕገ መንግሥቱ ለሴኔቱና ለሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት ጦርነት የማወጅ፣ የጦር ኃይልን የማስተዳደር፣ ግብር የመወሰን፣ ገንዘብ የመበደር፣ ገንዘብ የማተም፣ ንግድን የመቆጣጠርና መንግሥት ሥራውን እንዲሰራ የሚያስችሉትን አስፈላጊ ሕግጋት ሁሉ የማውጣት ኃላፊነት ይሰጣቸዋል።

ከውጭ መንግሥታት ጋር የሚደረጉ ስምምነቶችንና የባለሥልጣኖችን ሹመት በተመለከተ ምክር የመስጠትና የመቀበል ሥልጣን ያለው ሴኔቱ ብቻ ነው። በኢሌክቶራል ኮሌጅ ድምጽ አሰጣጥ ጊዜ እኩል ድምጽ ካጋጠመ የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት አሸናፊውን ፕሬዚደንት ይወስናል፤ ይህም በ1800 እና በ1824 በተካሄዱ ምርጫዎች በተግባር ታይቷል። የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት ባለሥልጣናት (ፕሬዚደንቱ ወይም ሌላ የፌዴራል መንግሥት ባለሥልጣን) የሚያስከስሳቸው ምክንያት አለ ብሎ የመወሰን ሥልጣን ያለው ሲሆን፣ በእንዲህ መልኩ እንዲከሰስ ውሳኔ የተሰጠበት ባለሥልጣን ለፍርድ የማቅረብ ወይም ከሥልጣኑ እንዲነሳ የመወሰኑ ሥልጣን ደግሞ የሴኔቱ ብቻ ነው።

## የአባላት ቢሮዎች

የአባላት ቢሮዎች በካፒቶል ደቡባዊ አቅጣጫ በኢንዲፔንደንስ ጎዳና ላይ ባሉ ሦስት ሕንጻዎች ውስጥ ይገኛሉ፤ ሕንጻዎቹም ዘ ካነን፣ ሎንግወርዝና ሬይበርን ይባላሉ። የሴኔተሮች ቢሮዎች ደግሞ በካፒቶል ሰሜናዊ አቅጣጫ በኮንስቲቲዩሽን ጎዳና ላይ ባሉ ሦስት ሕንጻዎች ውስጥ ይገኛሉ፤ ሕንጻዎቹ ራስል፣ ዲርክሰንና ሃርት ይባላሉ።

## የጎብኚዎች መረጃዎች

የካፒቶል ጉብኝት የሚጀምረው በኢስት ካፒቶል መንገድ ላይ ባለው አንደኛው መንገድ አጠገብ ወደሚገኘው የካፒቶል ጎብኚዎች ማዕከል ሲገቡ ሲሆን፣ በዚያም ጎብኚዎች ሁሉ በደህንነት ፍተሻ ሂደት ውስጥ ማለፍ አለባቸው።

የካፒቶል በአስጎብኚዎች የታገዘ ጉብኝት የሚጀምረው በካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል በታችኛው ደርብ ባሉት ከሁለቱ በአንዱ የመረጃ መስጫ አዳራሾች ነው። የ13 ደቂቃ ርዝመት ያለው "Out of Many, One" የተሰኘ ፊልም የዩኤስ ኮንግረስ እንዴት አዲስ ዓይነት መንግሥት እንደመሰረተ፣ ኮንግረስ በአሜሪካዊያን የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ የሚጫወተውን ሚና ከማብራራቱ በተጨማሪ የዩኤስ ኮንግረስ የሚገኝበትን ሕንጻ ለጎብኚዎች ያስተዋውቃል።



የሮተንዳው ጉብኝት ከሌሎች የካፒቶል ጉብኝት ሁሉ የላቀ ነው።

ጉብኝቶች ከክፍያ ነጻ ናቸው ሆኖም ግን የጉብኝት የይለፍ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። በwww.visitthecapitol.gov በሴኔተሮቻችሁ ወይም በተወካዮቻችሁ ቢሮዎች አማካኝነት ወይም በስልክ ቁጥር 202.226.8000 ለጎብኚዎች አገልግሎት ቢሮ በመደወል የጉብኝት ወረፋ መያዝ ይቻላል። በካፒቶል የጎብኝዎች ማእከል የተወሰኑ የጉብኝት ፈቃዶች በእለቱ ለት ሊኖሩ ይችላሉ።

ካፒቶልን በመጎብኘት ላይ ሳሉ የሴነተሮቻችሁንና እንደራሴዎቻችሁን ቢሮዎች ለመጎብኘት ወይም የእንደራሴዎች ምክር ቤት ወይም የሴኔት ምክር ቤት በስብሰባ ላይ ሳለ ለመገኘት ልትፈልጉ ትችላላችሁ። ወደ ምክር ቤቶቹ ለመግባት የጋለሪ ይለፍ ፈቃድ መያዝ ያስፈልጋል ይህም የይለፍ ፈቃድ ከሴነተሮችዎ ወይም ከእንደራሴዎ ቢሮዎች ማግኘት ይችላሉ። ዓለም ዓቀፍ ጎብኚዎች በካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል በላይኛውና ታችኛው ደርቦች በእንደራሴዎች ምክር ቤትና በሴኔት የቀጠሮ ዴስኮች ስለጋለሪ የይለፍ ፈቃድ መጠየቅ አለባቸው።

የካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል በታንክስ ጊቪንግ፣ በገና፣ አዲስ ዓመትና በበዓለ ሲመት ቀናት ካልሆነ በቀር ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ከ8፡30 a.m. እስከ 4:30 p.m. ክፍት ነው።

ጎብኚዎች ከጎብኚዎች ማዕከል ሠራተኞች ወይም በኢማኒሲፔሽን አዳራሽ ካሉ የመረጃ ዴስኮች ከአንዱ በእጅ የሚገፋ ተሽከርካሪ ወንበር መጠየቅ ይችላሉ። በቅድሚያ ወረፋ ከተያዘ የምልክት ቋንቋ አስገርጓሚዎች ማግኘት ይቻላል። ሁሉም ፊልሞች በስተግርጌአቸው የሚነገሩትን በፅሁፍ ያቀርባሉ።

ስለ ካፒቶል፣ የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤትና ስለሴኔት ተጨማሪ መረጃ በ www.aoc.gov፣ www.house.gov ና www.senate.gov ማግኘት ይቻላል።